# በመንግስት ሆስፒታሎች □ፅል ሕክምና አገልግሎት የአሰራር መመሪያ

2007 ዓ/ም


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia

Ministry of Health

This Publication is made possible by the support of United States Agency for International Development (USAID) through Health Sector Financing Reform/Health Finance & Governance (HSFR/HFG) Project which is part of the USAID's global Health Finance & Governance Project (HFG) Implemented by Abt Associates Inc. under cooperative agreement -AID-OAA-A-12-00080.

Ministry of Health

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE | Health Sector Financing Reform Project

HFG Health Finance & Governance Expanding Access. Improving Health.

# በመንግስት ሆስፒታሎች የግል ሕክምና አገልግሎት

# የአሰራር መመሪያ

ጤና ጥበቃ ሚ/ር

2007 ዓ/ም

ማውጫ


**መግቢያ ....... 1**

**ክፍል አንድ ....... 2**

**ጠቅላላ ድንጋጌ ....... 2**

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ ....... 2
አንቀጽ 2. ትርጓሜ ....... 2
አንቀጽ 3. አውጪው ባለስልጣን ....... 3
አንቀጽ 4. የመመሪያዉ ተፈጻሚነት ወሰን ....... 3
አንቀጽ 5. የመመሪያዉ አላማዎች ....... 3

**ክፍል ሁለት ....... 3**

**የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች ....... 4**

አንቀፅ 6. የግል ህክምና አግልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች ....... 4

**ክፍል ሦስት ....... 5**

**የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር ....... 5**

**አንቀጽ 7. የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም ....... 5**
7.1 ስለግል ህክምና አገልግሎት የማቋቋሚያ ውሳኔ ....... 5
7.2 ስለግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ ....... 5
7.3 መነሻ የሀብት ምንጭ ....... 6
7.4 የአገልግሎት ቅንጀት እና ስብጥር ....... 6
**አንቀጽ 8. የግል ህክምና አገልግሎት አደረጃጀት ....... 7**
**አንቀጽ 9. የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል አስተዳደር ....... 8**
9.1 በግል ህክምና አገልግሎት የሰራተኞች አመዳደብ ....... 8
9.2 የግል ህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት ....... 9

**መብትና ግዴታ ....... 10**

**አንቀጽ 10 የተገልጋዮች መብትና ግዴታ ....... 10**
10.1 የተገልጋዮች መብት ....... 10
10.2 የተገልጋዮች ግዴታ ....... 10
**አንቀጽ 11. የተቋሙ ግዴታዎች ....... 10**

**ክፍል አምስት ....... 11**

**ስለ የዋጋ ተመን፣ የገቢ ክፍፍል፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና ኦዲት ....... 11**

**አንቀጽ 12. የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የዋጋ ተመን ....... 11**
**አንቀጽ 13. የገቢ ክፍፍል ....... 11**
**አንቀጽ 14. የፋይናንስ አስተዳደር ....... 12**
14.1 የገቢ አሰባሰብና ክፍያ አፈጻጸም ....... 12
14.2 የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች ....... 13
14.3 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ....... 14
14.4 የኦዲት አገልግሎት ....... 14
14.5 የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ....... 14

**ክፍል ስድስት** ....... **16**

**ተግባር፣ ኃላፊነት እና ክትትልና ግምገማ** ....... **16**

- አንቀጽ 15. የጤና ጥበቃ ሚ/ር ተግባርና ኃላፊነት ....... 16
- አንቀጽ 16. የሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ ....... 16
- አንቀጽ 17. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ....... 17
- አንቀጽ 18. የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ ....... 18
- አንቀጽ 19. ክትትልና ግምገማ ....... 20

**ክፍል ሰባት** ....... **21**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** ....... **21**

- አንቀጽ 20. ተጠያቂነት ....... 21
- አንቀጽ 21. መመርያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ....... 22
- አንቀጽ 22. የተሻሩ መመሪያዎች ....... 22
- አንቀጽ 23. ተፈጻሚነት ....... 22

**ANEXES** **21**

አመልካቾች (INDICATORS) ....... 23

**COST OF PROVIDING SERVICES AND PROCEDURES IN PRIVATE WING AT HOSPITAL LEVEL** ....... **24**

**1. LABORATORY** ....... **24**

**2. MINOR SURGERY** ....... **25**

**3. NURSINGCARE &PROCEDURES** ....... **26**

**4. 4.MAJOR SURGERIES** ....... **27**

**5. OPHTHALMOLOGY PROCEDURES** ....... **28**

**6. DENTAL PROCEDURES** ....... **29**

**7. RADIOLOGY TEST** ....... **29**

**8. MISCELLANEOUS** ....... **31**

የግል ህክምና አገልግሎት የትርፍ ክፍፍል ....... 32

# መግቢያ

በሆስፒታሎች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀና በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል ሆስፒታሎች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 167/2001 ማጽደቁ ይታወቃል፡፡ ይህንኑ ደንብ ይበልጥ ለማብራራትና ተፈጻሚ ለማድረግ እንዲረዳ በማሰብ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በመንግሥት ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 001/2002 ማውጣቱ ይታወሳል፡፡

የዚህ አገልግሎት መጀመር የባለሙያዎችን የስራ ተነሳሽነት በመጨመርና ባሉበት ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ቆይተው እንዲያገለግሉ ከማስቻሉም በላይ ለህብረተሰቡ አማራጭ የህክምና አገልግሎት ሆኗል፡፡ይሁን እንጂ በአሠራሩ ላይ በተደረጉ ጥናቶች የአላቂ እቃዎች ለሆስፒታሉ የሚመለስ"በት ስርአት አለመኖር፣ የግል ህክምና አገልግሎት በመደበኛ የህክምና አገልግሎት ሰዓት መጀመር፣ የስው ሃይል አመዳደብ መርሆ አለመኖር፣ የአገልግሎት ዋጋ ወጥ ያለመሆን፣ የገቢ ትርፍ ክፍፍል ስርአት አለመኖር እና የመሳሰሉት ችግሮች የተስተዋሉ በመሆኑና ከተጠቃሚው ህብረተሰብ በሚነሱ ጥያቄዎች መሠረት ከዚህ በፊት በወጣው መመሪያው ያልተሸፈኑ ሁኔታዎችን ለማብራራትና የዋጋ ትመና ጣሪያ ለማስቀመጥ መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ ከሆስፒታል ሃላፊዎች እና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ከተደረገበት በኋላ ይህ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 167/2001 ለጤና ጥበቃ ሚኒስተር በተሰጠው ስልጣን የፌዴራል ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል፡፡

# <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

□ህ መመሪ□ «የፌዴራል ሆስፒታሎች □ፅል ሕክምና አገልግሎት የአሰራር መመሪያ» **ቁጥር 01/2007** ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

1. **"የግል ህክምና አገልግሎት"** ከድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ውጪ ከመደበኛ የህክምና አገልግሎት ጎን ለጎን ባለሙያዎች ከስራ ሰዓት ውጪና በበዓላት ቀን በተመጣጣኝ ክፍያ የተመላላሽና የተኝቶ ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ አገልግሎት ማለት ነው፡፡
2. **"የመደበኛ የሕክምና አገልግሎት ክፍል"** ማለት ሆስፒታሉ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለመደበኛ ሕክምና አገልግሎት ተገቢው የጤና ክብካቤ የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡
3. **"ማኔጅሜንት"** ማለት የሆስፒታሉ ማኔጅሜንት ማለት ነው፡፡
4. **"የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ"** ማለት ከተለያዩ የሆስፒታሉ ክፍሎች ከተውጣጡ ባለሙያዎች የሚመሰረትና የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን በሆስፒታሉ ውስጥ ለማቋቋም አዋጭነቱን በዝርዝር አጥንቶ የውሣኔ ሀሣብ የሚያቀርብ ቡድን ነው፡፡
5. **«ድንገተኛ ህክምና»** ማለት የወሊድ አገልግሎትን ጨምሮ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት ቅጽበታዊ እርዳታ የሚያሻው ያልተጠበቀና የከፋ የጤና መታወክ ሲያጋጥም የሚደረግ የህክምና አገልግሎት ነው፡፡
6. **"የአገልግሎት ጥራት"** ማለት የተገልጋዩን ህብረተሰብ የጤና አገልግሎት ፍላጎትና የተቀመጡ ስታንዳርዶች በተሟላ ደረጃ ተግባረዊ በማድረግ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ማለት ነው፡፡

7. “የፌዴራል ሆስፒታል” ማለት ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስተር የሆነ ሆስፒታል ወይም በዩኒቨርስቲ ስር የሚተዳደር የጤና አገልግሎት መስጫና የጤና ሙያ ማስተማሪያ ሆስፒታል ነው፡፡
8. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

## አንቀጽ 3. አውጪው ባለስልጣን

ይህንን መመሪያ ያወጣው ባለስልጣን የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ነው፡፡

## አንቀጽ 4. የመመሪያዉ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሁሉም የፌዴራል ሆስፒታሎች ላ□ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5. የመመሪያዉ አላማዎች

ይህ መመሪያ የሚከተሉትን አላማዎች ለማሳካት ያለመ ነዉ፡፡

5.1 የጤና ባለሙያዎች በትርፍ ጊዜያቸው ለሚሰጡት አገልግሎት ተጨማሪ ቁኢ እ□ዩኙ በጤና ተቋሙ ውስጥ እንዲቆዩ ማበረታታት፣ የስራ ተነሳሽነታቸውን ማሳደግና የሙያተኞችን ፍልሰት መቀነስ፡፡

5.2 የመክፈል አቅም ያላቸውን ተገልጋዮች በምርጫቸው የሚፈልጉትን የህክምና ባለሙያና የአገልግሎት አይነት በሚፈልጉት ሆስፒታል በሚመቻቸው ቀንና የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት እንዲያገኙ በማድረግ ተገልጋዮች በሚያገኙት አገልግሎት እንዲረኩ ማስቻል፡፡

5.2 ከግል ህክምና አገልግሎት በሚገኘው ተጨማሪ ገቢ በመጠቀም የመደበኛ አገልግሎትን ማሻሻል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች

### አንቀፅ 6. የግል ህክምና አግልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች

ሀ. የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጠው □መ□በኛውን አገልግሎት በማያስተጓጉልና በሚያጠናክር መልኩ መሆን አለበት::

ለ. ከምግብ፣ ከመኝታ □አሎች አገልግሎትና አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚፈጀው ቆ□ በስተቀር በመ□በኛውና በግል ህክምና አገልግሎት መካከል የአገልግሎት ጥራት ልዩነት መኖር የለበትም::

ሐ. የግል ህክምና አገልግሎቱ መቋቋም በመ□በኛ □ህ□ምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚሰጠውን የቀጠሮ ቆዜ ለማሳጠር የሚደረገውን ጥረት ማወክ የለበትም::

መ. በመ□በኛው የህክምና አገልግሎት ያልተጀመሩ ወይንም የማይሰጡ የህክምና አገልግሎቶች በግል ህክምና ክፍሉ መጀመር ወይም መሰጠት የለባቸውም::

ሠ. □መ□በኛ የህክምና አገልግሎትን ለመጠቀም የመጣን ወይም ህክምና እየተከታተለ ያለን ታካሚ በማንኛውም መልኩ የግል ህክምና አገልግሎትን እንዲጠቀም ተፅዕኖ ማድረግ የተከለከለ ነው::

ረ. በግል ህክምና አግልግሎት ህክምናውን እየተከታተለ ያለታካሚ ወደ መደበኛ ህክምና በበቂ ምክንያት ማዛወር ቢያስፈልግ የግል ህክምና አገልግሎት ኃላፊና የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር በመነጋገር ሊፈጸም ይችላል::

ሰ. በግል ህክምና አገልግሎት ስራ ላይ ያለ ባለሙያ ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ሲፈለግ ያለክፍያ የመስራት ግዴታ አለበት::

ሸ. የግል ህክምና አገልፅሎት የህክምና የቡድን አሰራር መንፈስን በተከተለ መልኩ የሚሰራ መሆን ይኖርበታል::

ቀ. የድንገተኛ ህክምና አገልግሎትን በግል ህክምና አገልግሎት □አል መስጠት የተከለከለ ነው::

## ክፍል ሦስት

## የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር

### አንቀጽ 7. የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም

### 7.1 ስለግል ህክምና አገልግሎት የማቋቋሚያ ውሳኔ

የግል የሕክምና መስጫ ክፍል ሊቋቋም የሚችለው በዚህ መመሪያ የተካተቱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የማቋቋሚያ ሀሳብ ሲቀርብ በሆስፒታሉ ማኔጅመንት በሚሰየም የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ የቴክኒክ ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ በሚካሄድ ጥናትና የሆስፒታሉ ሥራ አሥኪያጅ በሚያቀርበው የውሣኔ ሃሳብ መሰረት በሆስፒታሉ ቦርድ ተገምግሞ ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

### 7.2 ስለግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ

የግል ህክምና መስጫ አገልግሎትን በሆስፒታሉ ውስጥ የማቋቋም አዋጭነት በዝርዝር አጥንቶ የውሣኔ ሀሣብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው፡፡ ይህም ኮሚቴ በሆስፒታሉ ማኔጅመንት ይሰየማል፡፡ የግል ህክምና አግልግሎት ምስረታ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የሆስፒታሉን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም የግል ህክምና አገልግሎት አዋጭነትን ያጠናል፡፡

ለ. በግል ህክምና ክፍል ሊሰጡ የሚችሉ የጤና አገልግሎቶችን ይለያል፡፡

ሐ. የግል ህክምናውን ተግባር እና አላማ ለማሳካት የሚረዳ የገበያ ጥናት ያካሂዳል፡፡

መ. የሰው ኃይል ጥናት፣ የአሰራር ጥናትና የፋይናንስ ጥናት በማድረግ በወቅቱ የተለዩ ስጋቶችንና ታሳቢዎችን በዝርዝር ይለያል፡፡

ሠ. ከግል ህክምና ክንፍ የሚጠበቁ አገልግሎቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡

ረ. የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ የግል ህክምና አገልግሎቱ ሲጀመር የስራ ጊዜው ያበቃል፡፡

## 7.3 መነሻ የሀብት ምንጭ

7.3.1 የግል ህክምና መስጫ አገልግሎት ማቋቋሚያ ካፒታል የሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ምንጭ በተገኘ ካፒታል ሊቋቋም ይችላል፡፡

1. ከሆስፒታሉ መደበኛ የዉስጥ ገቢ ከሚገኝ ከወለድ ነጻ ብድር፣
2. ከመንግሥት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ እና
3. እንዳስፈላጊነቱ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ሊቋቋም ይችላል::

የግል ህክምና አገልግሎት ማቋቋሚያ ካፒታል ከሆስፒታሉ የዉስጥ ገቢ ወይም ከመንግሥት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ በብድር የተገኘ ከሆነ የብድሩ የመመለሻ ጊዜ በሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ ይወሰናል::

### 7.3.2 ስለ ቋሚ ንብረት

ለግል ህክምና አገልግሎት የተቋሙን ቋሚ ንብረት □ለ□አ□ መ□ቀም ይቻላል:: ሆኖም ግን የመደበኛውን አገልግሎት የማያስተጉል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ::

### 7.3.3 ስለ አላቂ ንብረቶች

ሀ/ የግል ህክምና መስ□ አገልግሎቱን ለመጀመር ሲወሰን የራሱ አላቂ ንብረቶች እንዲኖሩት ይደረጋል፧

ለ/ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሉ አላቂ ንብረቶችን በራሱ ማዘጋጀት ካልቻለ በተቋሙ እንዲቀርብ ይደረጋል:: ነገር ግን በግዥ ዕቅድ መካተቱንና በ□ወሩ የተጠቀመውን ቁሳቁስ ሂሳብ ለተቋሙ ገቢ እንዲያደርግ የሚያስችል □አሠራር መዘርጋትና ተፈፃሚንቱም ማኔፀመንት ማረፋቶጥ ይኖርበታል::

## 7.4 የአገልግሎት ቅንጅት እና ስብጥር

7.4.1. □ፅል ህክምና አገልግሎቱ በሆስፒታሉ እንዲጠቀምበት □ተ□ቀ□ለትን መሰረተ-ልማት እና የህክምና መሳሪያዎች ያለምንም ወቸ መ□ቀም □ችላል፧ሆኖም ፅን □ተሽከርካሪ አገልግሎት ወቹ በክፍያ ይሆናል::

7.4.2 የስራ ተያያዥነት ያላቸው የመደበኛ አገልግሎት ልዩ ልዩ ክፍሎች ከግል ህክምና አገልግሎት ጋር ተቀናጅተው መስራት አለባቸው::

**አንቀጽ 8. የግል ህክምና አገልግሎት አደረጃጀት**

ሀ. የጤና ተቋማት የግል ህክምና አገልግሎት በተመላላሽ ወ□ም/እና በተኝቶ ህክምና አገልግሎት ሊደራጅ ይችላል::

ለ. የግል ህክምና የተኝቶ ህክምና አገልግሎት ከመደበኛው የተኝቶ ህክምና አገልግሎት የተለየ ክፍል ያለው ሆኖ ከመደበኛው አጠቃላይ አገልግሎት አልጋ ከ10% የበለጠ መጠቀም አይችልም፡፡

ሐ. ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃልይ ለግል ህክምና አገልግሎት ከተመደበው አልጋ ውስጥ በመደበኛ አገልግሎት ባሉት ክፍሎች የሥራ ጫና አንፃር ይከፋፈላል።

መ. የግል ህክምና አገልግሎት የራሱ የሙሉ ጊዜ ኃላፊ እና ጸሐፊ/ ሪሴፕሽኒስት ይኖረዋል፤ የሰራተኞቹ የደመወዝ አከፋፈል በመንግስት የሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት ሆኖ ተጨማሪ እንደ አገልግሎቱ መጠን የማትጊያ ክፍያ በቦረዱ ዉሳኔ ይከፈላቸዋል። የግል ህክምና ክፍሉ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የማኔጅመንት ኮሚቴ አባል ሲሆን በቀጥታ የህሙማን ህክምና አግልግሎት ላይ አይሳተፍም።

## አንቀጽ 9. የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል አስተዳደር

### 9.1 በግል ህክምና አገልግሎት የሰራተኞች አመዳደብ

የሆስፒታሉ ማኔጅመንት፡-

ሀ. በመደበኛ አገልግሎት አሰጣጥ በእውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በተነሳሽነታቸው፣ በመደበኛ የሥራ ሰአት ባላቸው የሥራ ውጤትና በሙያ ስነ-ምግባራቸው የተሻሉ እና ፍቃደኝነታቸው እየታየ በግል ህክምና ክፍል ውስጥ በሚወጣው የሥራ ፕሮግራም መሰረት በየተራ እየተመደቡ እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

ለ. አንድ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት ሰዓት የሚሰጠው አገልግሎት በምጣኔ ሲሰላ በመደበኛ አገልግሎት ከሰጠው ግልጋሎት አንጻር አጠቃላይ በግል ህክምና አገልግሎት ያከናወናቸው ተግባራት ምዘና የመደበኛውን አገልግሎት ስልሳ በመቶ (60%) መብለጥ የለበትም፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም እንድያስችል የእያንዳንዱ ፈፃሚ ባለሙያ የግል የዕለት ሥራ አፈፃፀም መከታተያ መዝገብ (Log Book) በሆሰፒታሉ ይዘጋጅለታል፡፡

ሐ. በመደበኛ ህክምና ለተኙ ህክምና አገልግሎት የሚመደብ የሰው ኃይል መጠን በምጣኔ ለግል ህክምና አገልግሎት የተኙ ታካሚዎች መመደብ ይኖርበታል፡፡

መ. ማንኛውም በግል ህክምና አገልግሎት ለመሳተፍ የሚፈልግ ባለሙያ የኮንትራት ውል ከሆስፒታሉ ጋር መፈራረም ይኖርበታል፡፡

ሠ. በተመሳሳይ ሰዓት በመደበኛ ወይም በተረኝነት ተመድቦ የሚሰራ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት መመደብ የለበትም፡፡

ረ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኃላፊ በውድድር የሚመደብ ሲሆን በኃላፊነት የሚመደበው የጤና ባለሙያ ወይም ተያያዥነት ያለው ሌላ ባለሙያ፣ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪና የአራት አመት የሥራ ልምድ ሊኖረው ይገባል፡፡

ሰ. ተጨማሪ የግል ህክምና አገልግሎቶች ባለሙያ በኮንትራት በመቅጠር መመደብ ቢያስፈልግ የግል ህክምና ክፍል ግልጽ የማወዳደሪያ መስፈርት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ሸ. ለግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የጥበቃ፣ የጽዳት፣ ጠቅላላ አገልግሎት፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ ፋይናንስ፣ ግዥ፣ ስምሪት እና የመጋዘን የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ የሆስፒታሉን መደበኛ አገልግሎትን በማያስተጓጉል መልኩ መሆን አለበት፡፡

ቀ. በግል ህክምና ክፍል ውስጥ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ምደባ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ በዚሁ ንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ በተጠቀሰው መሰረት በዙርና በየተራ እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡

በ. የግል ህክምና አገልግሎት ለሚያከናውናቸው ሥራዎች በመደበኛው አገልግሎት የሚሰሩ ሰራተኞች አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

### 9.2 የግል ህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት

በግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት፡-

**1. ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ሰአት**

ሀ. ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ ከሥራ ሰዓት ውጭ ከ11፡00 እስከ ምሽቱ 4፡00 ይሆናል፡፡

ለ. ዘወትር ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በሕዝባዊ በዓላት ወቅት ከጠዋቱ 2፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ይሆናል፡፡

ሐ. በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በወረፋ ብዛት አልያም የሚከናወነው ፕሮሲጀር ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ የተጠቀሰው የሥራ ሰዓት በእለቱ ብቻ ሊራዘም ይችላል፡፡

**2. ለተኝቶ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት**

ሀ. የነርሲንግና የሐኪም ክትትል አገልግሎት በግል ህክምና ክፍል በተመደቡ ሰራተኞች ብቻ ለ24 ሰዓት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ለ. የቀዶ ጥገና አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ በተጠቀሰው ሰዓት ብቻ መሆን አለበት፡፡

# ክፍል አራት

## መብትና ግዴታ

### አንቀጽ 10 የተገልጋዮች መብትና ግዴታ

### 10.1 የተገልጋዮች መብት

**አጠቃላይ የሆስፒታል ተገልጋይ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ**

ሀ. በተቻለ አቅም አጭርና የተመቻቸ የህክምና ቀ□ሮ ማፅኘት

ለ. ተፀልፉ□ በ□ለፀዉ ባለሙ□ □መታከም

ሐ. ተገልጋዩ ከአሎ ካርድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ ለተመሳሳይ የህክምና ችግር ለተከታታ□ 7 ቀናት ያለተጨማሪ የካርድ ክፍያ □ህክምና አገልግሎቱን ማፅኘት

መ. በግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጠውን የአገልግሎት ዝር□ር፣ዋጋ እና የባለሙያዎች የሙያ ደረጃ ፣የስራ ልምድና ብቃት የማወቅ

ሠ. ለታከመው ህክምና በፅሁፍ የሀኪም ማስረጃ የማግኘት

### 10.2 የተገልጋዮች ግዴታ

ሀ. □መ□በኛዉና የግል ህክምና አገልግሎቱን ህግና ደንብ ማክበር፣

ለ. የህክምና ስነ-ምግባርን ከሚጋፉ ድርጊቶች መቆጠብ፣

ሐ. ለግል ህክምና አገልግሎት የተተመነውን ቅድሚያ ክፍያ መፈፀምና አገልግሎቱን ሲጨርስ ሂሳቡን ማወራረድ፣

### አንቀጽ 11. የተቋሙ ግዴታዎች

ሀ. በግል ህክምና የሚሰ□ዉ አገልግሎት በመደበኛውም አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ማሳወቅ፣

ለ. የተሻለ የአገልግሎት አቅርቦት እንደ ምግብ፤ አልጋና ሌሎች አገልግሎቶች □ማቅረብ፣

ሐ. በመ□በኛውም ሆነ በግል ህክምናው የሚሰጠው አገልግሎት በጥራቱ ተመሳሳይ መሆኑን ማሳወቅ፣

መ. ሁሉንም አይነት የአገልግሎት ዋጋ ተመን ግልጽ በሆነ ቦታ መለ□ጠፍ፣

ሠ. ሀኪሞች ሙሉ ስማቸውን፤ የሙያ አይነትና አገልግሎት የሚሰጡበትን ቀን በፅልን መለ□አ፤

ረ. አገልግሎቱ በሆስ□ታሉ በመ□በኛዉ አገልፅሎት እስካልተሰ□ ትረስ በግል ህክምና □ኣሉ እንዳይሰጥ ማድረግ፤

ሰ. በግል ህክምናው አገልፅሎት ተመድበው □ሆስ□ታሉ ሰራተኞች በመስራት ላይ □ሉ በተለያዩ ምክንያቶች ስራ ሲ□ስተጃቶሉ □መ□በኛውን ስራ እንደበ□ሎ ተቆዓሮ አስ□ላቂዉን □ኡርምት እርምጃ መዉሰት፤

ቀ. አገልግሎቱ በ□ህ መመሪ□ በተፈቀደው ሰዓት ብቻ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣

## ክፍል አምስት

## ስለ የዋጋ ተመን፣ የገቢ ክፍፍል፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና ኦዲት

### አንቀጽ 12. የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የዋጋ ተመን

ሀ. በግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ታካሚው ለተሰጠው አገልግሎት የሚከፍለው የክፍያ ታሪፍ በታካሚው ላይ ከፍተኛ ጫና በማይፈጥርና ለባለሙያዎች ተመጣጣኝ ገቢ በሚያስገኝ አግባብ ሆኖ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከተዘጋጀው የአገልግሎት ክፍያ ጣሪያ መብለጥ የለበትም፡፡ (ዝርዝሩ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኗል)

### አንቀጽ 13. የገቢ ክፍፍል

ከሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ጠቅላላ ገቢ ላይ የአላቂ መገልገያ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ከአገልግሎቱ የተገኘ ትርፍ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ከተጣራው የግል ህክምና ገቢ 70% ለጤና ባለሙያ 15% ለሆስፒታል እና ቀሪው 15% ለአስተዳደርና ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይውላል፡፡ ከሁሉም እኩል 1 አንድ በመቶ ተቀንሶ 3% የግል ህክምና ክፍል ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ሀ. የባለሙያዎቹ ድርሻ የሆነው 69% የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ በሥራው ላይ ያለው ተፈላጊነትና ያሳለፈውን የሥራ ሰዓት ባገናዘበ መልኩ እንደ ሆስፒታሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ በሚወጣ የግል ህክምና አገልግሎት የገቢ ክፍፍል ቀመር መሰረት በቦርድ በማፀደቅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ለ. ለአስተዳደርና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ድርሻ ከሆነው 14% ውስጥ የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ብር 2000-2500፣ ሜዲካል ዳይሬክተር ብር 1500-2000 እና የግል ህክምና አገልግሎት ኃላፊው ብር 2000-2500 የማትግያ ክፍያ እንደ ሆስፒታሉ የገቢ መጠን ይከፈላቸዋል፤፤እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች ክፍያ በቁርጥ የሚወሰን ሆኖ ቀሪው ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በቀመር ይከፋፈላል፡፡ የቁርጥ ክፍያ መጠንና እና የአከፋፈል ቀመር በሥራ አመራር ቦርድ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ሐ. በግል ህክምና አገልግሎት ስም ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀመጠው 3% ገቢ የግል ህክምና አገልግሎቱን ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ገንዘቡን ለመጠቀም እቅድ ሲያቀርብና የሥራ አመራር ቦርዱ ሲያፀድቀው ገንዘቡ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፣

መ. ከግል ህክምና አገልግሎት የሚገኘው 14% የሆስፒታሉ ድርሻ በቦርዱ ውሣኔ ሁለንተናዊ የሆስፒታሉን አገልግሎት ጥራት ለሚያሻሽሉ ተግባራት የሚውል ይሆናል።

ሠ. ከላቦራቶሪ እና ዲያግኖስቲክስ አገልግሎት የሚገኝ ትርፍ የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ ባለሙያዎች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ወደ ጥል ገብቶ የሚከፋፈል ሲሆን ማንኛውም ሀኪም ካዘዘው የላቦራቶሪ ወይም የዲያግኖስቲክስ ምርመራ አገልግሎት ክፍያ በቀጥታ ገቢ ሊያገኝ አይገባም፡፡

ረ. ከላይ በአንቀፅ 13 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የገቢ ክፍፍል ቀመር ሲያፀድቅ በዚህ መመሪያ አባሪ የተደረገውን የግል ህክምና አገልግሎት የትርፍ ክፍፍል መነሻ በማድረግ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14. የፋይናንስ አስተዳደር

### 14.1 የገቢ አሰባሰብና ክፍያ አፈጻጸም

ሀ. ለግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚፈጸሙ ክፍያዎች፤ግዥዎችና የንብረት አስተዳደር ሥራዎች የመንግስት የፋይናንስ መመርያን የተከተሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

ለ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚሰበሰበዉ ገቢ በሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት ስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ምዝገባና ፈቃድ በሚታተም ደረሰኝ ይሆናል፡፡

ሐ. የሚሰበሰበዉ ገቢ ለየግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት እንዲዉል በሚከፈት ልዩ የባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ይደረጋል፡

መ. ገቢዉ ለዚሁ አገልግሎት በሚመደቡ የዕለት ገቢ ሰብሳቢዎች አማካኝነት የሚሰበሰብ ሲሆን ወደ ባንክ ገቢ እስኪሆን ድረስ በአስተማማኝ ካዝና እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

ሠ. የባንክ ሂሳብ ማንቀሳቀስ የሚቻለው

1. በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊና በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ጣምራ ፊርማ ወይም
2. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ በሌለ ጊዜ በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊ እና የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

## 14.2 የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች

ሀ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች ሆስፒታሉ የሚሰጣቸዉ

- የተመላላሽና የተኝቶ ህክምና አገልገሎት፤
- የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ አገልግሎቶች
- የምግብ እና የመኝታ አገልግሎት
- የጤና ምርመራ ማስረጃ (medical certificate) አገልግሎት እና
- ሌሎች በግል ህክምና የሚሰጡ ተጓዳኝ የህክምና አገልግሎቶች ይሆናሉ፡፡

ለ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢ ከመድኃኒትና ከአላቂ የህክምና መገልገያ እቃዎች ሽያጭ የሚገኘን ገቢ አያጠቃልልም፡፡

ሐ. ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸዉ የግል ህክምና አገልግሎቶች የሚገኘዉ ገቢ ለክፍያ አፈጻጸምና በግልጽ ለሚቀርብ የፋይናስ ሪፖርት አጋዥ ይሆን ዘንድ ለየገቢ ምንጩ ኮድ እንዲኖረዉ ይደረጋል

መ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረስ ስምምነት መሰረት የዱቤ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

### 14.3 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ

ሀ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የራሱ የሆነ የሂሳብ መዝገብ፣ የባንክ ሂሳብ፣ የገቢ ደረሰኝና ልዩ ልዩ ቅጻቅጾች ከመደበኛዉ ሂሳብ ተለይተዉ ይኖሩታል፡፡

ለ. ማንኛዉም የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢና ወጪ በየዕለቱ መመዝገብ አለበት፡፡

ሐ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚጠቀምባቸዉ የሂሳብ ሰነድ ዓይነቶች ይዘት በመደበኛዉ አገልግሎት ሥራ ላይ የሚዉሉት አይነት ይሆናሉ፡፡

መ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢና ወጪዎች በሂሳብ መዝገብ በአግባቡ ተመዝግቦ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

ሠ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሂሳብ አያያዝ የሀገሪቱን የሂሳብ አያያዝ አዋጅ፡ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

### 14.4 የኦዲት አገልግሎት

ሀ. የሆስፒታሉ የዉስጥ ኦዲተር ስለየግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎትና የሂሳብ አያያዝ ለሆስፒታሉ ሥራአስኪያጅ ክትትል በማድረግ ያማክራል፣ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ለ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ ቢያንስ በሩብ አመት አንድ ጊዜ በዉስጥ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

ሐ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በዉጭ ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፡፡

መ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ የሚመረመረዉ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

### 14.5 የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ

14.5.1 የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት ሂሳብ በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በአመት ለሆስፒታሉ ሥራአስኪያጅና ለሌሎች ለሚመለከታቸዉ አካላት በወቅቱ መቅረብ አለበት፡፡

14.5.2 የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የፌደራል መንግስት የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያሳትማቸው የሂሳብ ማቅረቢያ ፎርሞችን በመጠቀም፡፡

1. የገቢ ሪፖርት
2. የወጪ ሪፖርት
3. የተሰብሳቢ ሪፖርት
4. የተከፋይ ሪፖርት
5. የሂሳብ ሚዛን
6. ሳጥን ሂሳብ ሪፖርት
7. የባንክ ማስታረቂያ
8. የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ወዘተ… ርፖርት መቅረብ አለበት፡፡

14.4.1 የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት አጠቃላይ አመታዊ ሪፖርት ለሆስፒታሉ ማኔጅመንትና ለቦርዱ ቀርቦ መገምገምና መጽደቅ ይኖርበታል።

## ክፍል ስድስት

## ተግባር፣ ኃላፊነት እና ክትትልና ግምገማ

### አንቀጽ 15. የጤና ጥበቃ ሚ/ር ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

ለ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዳል፣የአሰራር ማሻሻያ ያደርጋል፡፡

ሐ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ መልካም ተሞክሮችን ይቀምራል፣ ያሰፋል፡፡

መ. ለግል ሕክምና አገልግሎት ማጠናከሪያ የሚሆን ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሠ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ መከታተያና መገምገሚያ መስፈርት ያወጣል አሰራሩን ለማጠናከር የሚያስችል የድጋፋዊ ክትትል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

ረ. ስለግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ የሚቀርብለትን የአፈፃፀም ሪፖርቶች ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

### አንቀጽ 16. የሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ

ሀ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም በቀረበው ሰነድ ላይ ተወያይቶ ክፍሉ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

ለ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ተግባር በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ሐ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን በተመለከተ የሚከናወኑ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በበላይነት ይደግፋል፡፡

መ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ ምደባ በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ይወስናል፡፡

ሠ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን የመነሻ ካፒታል መጠንና ምንጭ ይወስናል፡፡

ረ. በዚህ መመሪያ የወጣውን የክፍያ ማዕቀፍ መሰረት አድርጎ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል የአገልግሎት ክፍያ ተመን መፈጸሙን ይከታተላል፡፡

ሰ. የግል ህክምና አገልግሎትን የገቢ ክፍፍል ቀመር ያጸድቃል፤ይከታተላል፡፡

ሸ የግል ሕክምና አገልግሎት አስተዋፅኦና የአገልግሎት አሰጣጡ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ይገመግማል፤ ይከታተላል፡፡

ቀ. የግል ሕክምና ክፍሉን አስመልክቶ የቀረበውን የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ አመትና አመታዊ ሪፖርቶችን ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

በ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን አመታዊ እቅድና በጀት ገምግሞ ያፀድቃል፡፡

ተ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፡፡

## አንቀጽ 17. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ

ሀ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለመቋቋም የሚያስችል ጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ከማኔጅመንቱ ጋር በመሆን ይመርጣል ይሰይማል፡፡

ለ. በጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ተጠንቶ የቀረበውን ጥናት ገምግሞ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

ሐ. የወጣውን መስፈርት መነሻ በማድረግ ማኔጅመንቱን ባሳተፈ ሁኔታ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ በመምረጥ ለሥራ አመራር ቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

መ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ያለውን ሥራ ለማከናወን የሚያግዙ ጊዚያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

ሠ. የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን ለማስጀመር፣ ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን ሀብት ያፈላልጋል፡፡

ረ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ለመከታተል የሚያስችል ቼክሊስት ያዘጋጃል፣ በዚሁ መሰረት ክትትል ያደርጋል የማሻሻያና የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

ሰ. የግል ሕክምና አገልግሎት ከመደበኛ አገልግሎት ጋር የተቀናጀ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሸ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ በየወቅቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት ገምግሞ ለሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል፡፡

ቀ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያስተባብራል፡፡

በ. በግል መስጫ ክፍሉ ውስጥ ስለሚሰጠው የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበል በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ተ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፤ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

ቸ. በሆስፒታሉ ሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 18. የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ

ሀ. በግል ህክምና አገልግሎት ውስጥ የሚከናወኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፣ አግባብ ያለው የሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተግባር መፈፀሙን ያረጋግጣል፤በሂሳብ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ የቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ገምግሞ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

ለ. የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበልን በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላል፣ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ሐ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረጉ የተተመኑ ወይም የተከለሱ የአገልግሎት ክፍያዎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፡

መ. በየጊዜው ክትትል በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ በማደረግ ሙስና፣ ብክነትና ምዝበራ እንዳይፈጠር ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

ሠ. በግል የሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሰራተኞችን ይመድባል፣ የተመደቡ ሰራተኞችን ዝርዝር በግልፅ ቦታ በመለጠፍ ሰራተኞች እንዲያውቁት ያደርጋል፣ ሰራተኞች በምድብ ቦታቸው ተገኝተው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በወሩ መጨረሻም አስፈላጊውን መረጃ ለሂሳብ ክፍል ያስታውቃል፡፡

ረ. በግል የህክምና መስጫ ክፍል ከሚሰጡ አገልግሎቶች የሚሰበሰቡ ገቢዎችና የሚፈፀሙ ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሠረት መከናወናቸውን በመከታተል ለማኔጅመንት ኮሚቴና ለሥራ አመራር ቦርዱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

ሰ. መደበኛና ድንገተኛ ኦዲት በባለሙያዎች በማካሄድ የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጡ የታለመውን አላማ ያሳካ ስለመሆኑ ይገመግማል፡፡

ሸ. በግል የህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሚሠጡ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሥራ ውል እንዲፈራረሙ በማድረግ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

ቀ. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ ስለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

በ. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት በመደበኛ የህክምና ክፍሉ ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣ ተመሳሳይነቱንም ይከታተላል፣ ልዩነት ሲፈጠር የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

ተ. ለግል ሕክምና ክፍሉ የሚያስፈልጉ ግብኣቶችን በመለየት ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄ ያቀርባል፣ የተጠየቁት ግብአቶች ተሟልተው መቅረባቸውን ይከታተላል፡፡

ቸ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ አዳዲስ የሕክምና አገልግሎቶችን ለማስጀመር ጥያቄ ሲቀርብ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማማከር አዳዲስ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ የውሳኔ ሀሳብ ለሥራ አስኪያጁ ያቀርባል፡፡

ነ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ወርሃዊ የሩብ ዓመትና አመታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

ኘ. በየሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 19. ክትትልና ግምገማ

የግል ህክምና አገልግሎት አሠራር እና ጥራት ላይ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ በክትትል እና ግምገማ ሥራውም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤ የሆስፒታል ቦርድ፤ የግል ህክምና ክፍል፤ የሆስፒታል ማኔጅመንት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራሉ፡፡

ለዚህ ግምገማ እና ክትትል የሚያስፈልጉ የመረጃ ምንጮች በሆስፒታሉ ከሚገኝ መረጃና በHMIS ከሚጠናቀር ሪፖርት ይሆናል፡፡ ክትትልና ግምገማ በተዘጋጀ ቼክሊስት እና በተመረጡ አመላካቾች (Indicators) የወር፣ የሩብ አመት፣ የግማሽ አመት እና የአመት ሪፖርት በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፡፡ በተዋረድም ሪፖርትቱን በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጣል ድጋፋዊ ክትትልም በየጊዜው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 20. ተጠያቂነት

20.1 ማንኛውም የግል ህክምና የሚሰጥ የፌደራል ሆስፒታል ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

20.2 በዚህ መመርያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓቶችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሆስፒታል እንደ ጥፋቱ ሁኔታና ክብደት እየታየ የግል ህክምና አግለግሎቱን መዝጋት ጨምሮ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

20.3 ማንኛውም በግል ህክምና ክፍል ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ እና የሥራ ኃላፊ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓት የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

20.4 በዚህ መመርያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓቶችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰራተኛ እና የሥራ ኃላፊ እንደጥፋቱ ሁኔታና ክብደት እየታየ ከግል ህክምና ክፍሉ ከመታገድ ጀምሮ በመንግስት የሲቪል ሰርቪስ ህግና በሀገሪቱ መደበኛ የፍትህ ስርዓት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 21. መመርያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 22. የተሻሩ መመሪያዎች**

በመንግስት ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት አሰራርና የአደረጃጀት መመርያ ቁጥር 001/2002 በዚህ መመርያ ተሽሯል፡፡

**አንቀጽ 23. ተፈጻሚነት**

ይህ መመሪያ ከሚያዚያ 01/2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ 11/7/2007 ዓ.ም

Signature: Kesete-birhan Admasu Birhane (Dr.
Minister
Date: March 11, 2015

ከሰተብርሃን አድማሱ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስትር

## ANEXE

### አመልካቾች (Indicators)

የሚከተሉት አመልካቾች የዚህን ኘሮግራም ውጤታማነት ለመገምገምና ለመከታተል ይውላሉ።

| ተ.ቁ | አመልካቾች(Indicators) | ሪፖርት የማድረጊያ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የመደበኛ ተመላላሽ ታካሚዎች ቁጥር ከግል ህክምና ተመላላሽ ታካሚዎች ቁጥር በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 2 | የመደበኛ የተኝቶ ታካሚ ቁጥር ከግል ህክምና የተኝቶ ታካሚ ቁጥር በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 3 | ከሆስፒታሉ ምን ያህሉ አልጋ ለግል ህክምና አገልግሎት ተመድቧል | በየሩብ አመቱ |
| 4 | በሆስፒታሉ ካሉ ስፔሻሊስት ሐኪሞች ምን ያህሉ በግል ህክምና አገልግሎት ይሳተፋሉ፣ | በየሩብ አመቱ |
| 5 | የስፔሻሊስቶች Attrition Rate: ከሆስፒታሉ የሚለቁ የስፔሻሊስት ሐኪሞች ብዛት መጀመሪያ ከነበረው የስፔሻሊስት ሐኪሞች ቁጥር ተካፍሎ በመቶኛ ይሰላል፣ | በየስድስት ወሩ |
| 6 | በመደበኛ የሥራ ቀናት አንድ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት ሰዓት የሰጠው አገልግሎት እና መደበኛ አገልግሎት ስዓት ከሰጠው አገልግሎት በምጣኔ፣ | በየወሩ |
| 7 | ሆስፒታሉ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ ምን ያህሉ የግል ህክምና አገልግሎት ድርሻ ነው፣ | በየሩብ አመቱ |
| 8 | የመደበኛ ተኝቶ ታካሚ የቆይታ ጊዜ በአማካይ ከግል ህክምና ተኝቶ ታካሚ የቆይታ ጊዜ በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 9 | በግል ሕክምና አገልግሎት ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞች እርካታ፣ | በየስድስት ወሩ |
| 10 | በግል ሕክምና አገልግሎት ከተጠቀሙ ህሙማን የአገልግሎት እርካታ፣ | በየስድስት ወሩ |

# Cost of Providing Services and Procedures in Private Wing at Hospital Level

## 1. Laboratory

**ማሳሰቢያ፡-** ተገልጋዩ በቀጥታ ከሚከፍላው የግል ህክምና አገልግሎት ክፍያ (PW price) ላይ የአላቂ እቃዎች ዋጋ (PW supply cost) ተቀንሶ ለሆስፒታሉ ገቢ ከተደረገ በኋላ ቀሪው በግል ህክምና አገልግሎት የተገኘ ትርፍ ይሆናል፡፡

| No. | Services | PW Price | Estimated supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | AFB | 15 | 7 |
| 2. | ASO titer | 24 | 12 |
| 3. | B/F | 10 | 7 |
| 4. | Blood Group | 20 | 13 |
| 5. | Body fluid analysis (peritoneal, synovial, plural, etc | 40 | 28 |
| 6. | CBC | 25 | 7 |
| 7. | Cervical mucus analysis | 12 | 6 |
| 8. | Cholesterol | 20 | 10 |
| 9. | CSF analysis | 32 | 23 |
| 10. | ESR | 13 | 7 |
| 11. | FBS/RBS | 10 | 7 |
| 12. | Fungs scraping/koh/ | 15 | 8 |
| 13. | Gram stain | 21 | 12 |
| 14. | H. Pylory | 31 | 9 |
| 15. | HBSAg | 25 | 9 |
| 16. | HCT | 10 | 4 |
| 17. | HCV | 30 | 11 |
| 18. | HGB | 7 | 2 |
| 19. | L.F.T (Got ,GPT,ALP) | 50 | 18 |
| 20. | Pregnancy Test | 15 | 7 |
| 21. | R. F.T (urea & creatinine) | 28 | 13 |
| 22. | RBC morphology/peripheral blood morphology | 15 | 7 |

| No. | Services | PW Price | Estimated supply cost |
|---|---|---|---|
| 23. | Rheumatoid Factor (RF) | 19 | 9 |
| 24. | RPR | 17 | 9 |
| 25. | Skin snip | 24 | 9 |
| 26. | Sperm analysis | 39 | 18 |
| 27. | Stool Direct | 10 | 6 |
| 28. | Triglycerides | 15 | 6 |
| 29. | U/analysis Test | 17 | 10 |
| 30. | Uric Acid | 18 | 6 |
| 31. | VDRL | 17 | 9 |
| 32. | WBC | 10 | 5 |
| 33. | Weil flix | 14 | 7 |
| 34. | Wet Smear | 20 | 10 |
| 35. | Widal | 21 | 10 |
| 36. | X-match | 18 | 9 |
| 37. | Hormonal assay | 120 | 40 |

## 2. Minor Surgery

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abscess drainage | 51 |
| 2. | Anal dilation (large) | 339 |
| 3. | Anal Dilation (simple) | 176 |
| 4. | Bouginage | 89 |
| 5. | Breast Lump removal | 336 |
| 6. | Cauterization | 384 |
| 7. | Chest tube insertion | 244 |
| 8. | Chest tube removal | 40 |
| 9. | Circumcision | 133 |
| 10. | Cystostomy | 250 |
| 11. | Dressing surgical wound | 60 |
| 12. | Fibro adenoma excision | 341 |
| 13. | Gastric lavage | 54 |

| | | |
|---|---|---|
| 14. | Hydrocelectomy | 518 |
| 15. | Ingrowth toe-nail excision | 349 |
| 16. | Intra-articular injection | 181 |
| 17. | Lipoma/ganglion/dermoidcyst excision (big ) | 344 |
| 18. | Long arm Cast | 174 |
| 19. | Long leg cast | 239 |
| 20. | Lumbar puncture | 95 |
| 21. | Lymph node biopsy | 134 |
| 22. | Paracenthesis/therapeutic | 88 |
| 23. | Pericardiosynthesis | 160 |
| 24. | Peritoneal fluid taping | 23 |
| 25. | Rectal Tube deflation | 4 |
| 26. | Removal of cyst/lipoma(simple) | 245 |
| 27. | Removal of Foreign Body from Ear and Nose | 214 |
| 28. | Short leg cast | 141 |
| 29. | Simple & incisional biopsy | 329 |
| 30. | Supply of Oxygen inhalation/hr | 10 |
| 31. | Thoracentesis(diagnostics) | 55 |
| 32. | Thoracentesis (therapeutic) | 91 |
| 33. | Urethral or bladder irrigation | 19 |

## 3. NURSINGCare &Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Nursing care for non-bedridden patients per day | 60 |
| 2. | Nursing care for post-surgery per day | 80 |
| 3. | Nursing care for bedridden patient per day | 80 |
| 4. | Nursing care for comatose patient per day | 100 |
| 5. | Application of Cast | 47 |
| 6. | Colostomy Irrigation (Care) | 20 |
| 7. | Ear Irrigation | 19 |
| 8. | Enema | 25 |
| 9. | NGT Insertion | 13 |
| 10 | Perennial Care | 10 |
| 11 | Post Mortem Care | 100 |
| 12 | Removal of Cast | 15 |
| 13 | Stich Removal | 10 |

## 4. 4.Major Surgeries

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abdomino-perineal resection of bowel | 2,688 |
| 2. | Barthelin's abscess | 500 |
| 3. | Big mass excision with GA | 2,605 |
| 4. | Bone marrow aspiration with GA | 900 |
| 5. | Cerclage | 752 |
| 6. | Thoracic Surgery | 2,988 |
| 7. | Cholecystectomy (Complicated) | 3,090 |
| 8. | Cholecystectomy (Simple) | 2,704 |
| 9. | Clitoral cyst. big with anesthesia | 1,680 |
| 10. | Club foot correction | 1800 |
| 11. | Colostomy Cloture (Complicated) | 3,170 |
| 12. | Colostomy Cloture (Simple) | 2,588 |
| 13. | Complicated fracture with debridement | 2,100 |
| 14. | Cystolithomy(stone removal from urinary bladder) | 2,373 |
| 15. | Depressed skull fracture Burr hole elevation | 2,556 |
| 16. | Dislocation/Closed reduction | 1,792 |
| 17. | Dislocation/open correction (Elective) | 2,619 |
| 18. | D and C | 742 |
| 19. | Elective Caesarian Section | 1,637 |
| 20. | Finger Amputation | 1,432 |
| 21. | Fistuloctomy expect obstetric | 2,342 |
| 22. | Gasterojejinoostomy with vagotomy | 2,736 |
| 23. | Goo-Vagotomy | 2300 |
| 24. | Hemorrhoidectomy | 2,257 |
| 25. | Hernorrhaphy with general anstesia | 2,007 |
| 26. | Hernorrhaphy with local Anstesia | 1,338 |
| 27. | Imperforated anus (Specify cut back) | 2,302 |
| 28. | Imperforated anus (Simple) | 1800 |
| 29. | Imperforated hymen | 654 |
| 30. | Laparotomy | 2,636 |
| 31. | Lower Limb Amputation | 2,271 |
| 32. | Mastectomy (Radical) | 2,958 |
| 33. | Mastectomy (Simple) | 2,588 |
| 34. | MVA(Manual Vacuum Aspiration) | 504 |
| 35. | Myomectomy | 1,830 |
| 36. | Nephrectomy | 2,967 |
| 37. | Nephrolithotomy anduretero-lithotomy | 2,568 |
| 38. | Other gastro intestinal major surgery | 2,740 |
| 39. | Other major urologic surgeries | 2,807 |
| 40. | Other Major orthopedics surgery | 3,500 |
| 41. | Other major neurosurgical procedures | 3,950 |

| | | |
|---|---|---|
| 42. | Ovarian cyst. Removal big | 2,470 |
| 43. | Ovarian cyst. Removal small | 1,664 |
| 44. | Prostatectomy simple | 2,443 |
| 45. | Prostatectomy complicated | 2,968 |
| 46. | Redundant sigmoid volvulus resection & anastomosis | 2,662 |
| 47. | Repair of Ligaments and other plastic surgery | 2,680 |
| 48. | Repair of Tendons | 2,691 |
| 49. | Sequestrectomy (General) | 2,548 |
| 50. | Sequestrectomy /local/ | 1,700 |
| 51. | Thyroidectomy (Sub-total) | 2,534 |
| 52. | Thyroidectomy (Total) | 2,896 |
| 53. | Varicose vein milking and ligation | 2,300 |

## 5. Ophthalmology Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Capsulotomy /squint | 622 |
| 2. | Chelazion/curettage | 897 |
| 3. | Conjunctiva tear | 1,192 |
| 4. | Corneal tear | 1,581 |
| 5. | Correction of intropion | 1,117 |
| 6. | Dressing for corneal ulcer | 670 |
| 7. | ECCE | 2,293 |
| 8. | ECCE +PC IOL | 1,672 |
| 9. | Evisceration | 901 |
| 10. | Glaucoma operation | 1,756 |
| 11. | ICCE | 2,293 |
| 12. | ICCE + AC IOL | 1,878 |
| 13. | Inoculation | 889 |
| 14. | Lid repair | 913 |
| 15. | Lid tumor excision | 1,820 |
| 16. | Probing | 683 |
| 17. | Pterrigium removal | 1,042 |
| 18. | Scleral operation | 1,756 |
| 19. | Scleral Operation | 1,753 |
| 20. | Scleral tear | 1,581 |
| 21. | Skin Graft Release of Scar | 1,820 |
| 22. | Strabotomy/squint | 1,893 |
| 23. | Sub-conjunctiva injection | 694 |
| 24. | Tarsal picking/bilateral | 721 |
| 25. | Tarsotomy | 1,047 |

## 6. Dental Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abscess tooth drainage | 312 |
| 2. | Alveolar bone fracture/splitting | 1,102 |
| 3. | Amalgam filing | 467 |
| 4. | Composite resin filling | 779 |
| 5. | Excision of periodontitis | 767 |
| 6. | Preapicalaspextomy | 775 |
| 7. | Root canal filling | 761 |
| 8. | Splinting | 807 |
| 9. | Supra & sub gingival(calculus scaling) | 757 |
| 10. | Surgical extraction | 760 |
| 11. | Temporary filling | 856 |
| 12. | Tooth extraction | 463 |
| 13. | Ultrasonic scaling | 775 |
| 14. | With arch bar & wire | 1,113 |

## 7. Radiology Test

**ማሳሰቢያ፡-**ተገልጋዩ በቀጥታ ከሚከፍላው የግል ህክምና አገልግሎት ክፍያ (PW price) ላይ የአላቂ እቃዎች ዋጋ (PW supply cost) ተቀንሶ ለሆስፒታሉ ገቢ ከተደረገ በኂላ ቀሪው በግል ህክምና አገልግሎት የተገኘ ትርፍ ይሆናል፡፡

| No | Services | PW Price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | Abdomen/Plain/adult | 60 | 20 |
| 2. | Abdomen/Plain/Infant | 50 | 10 |
| 3. | Barium Enema | 81 | 27 |
| 4. | Barium Meal Follow through | 111 | 37 |
| 5. | Ba-Swallow | 93 | 31 |
| 6. | Ba-Swallow with caster oil | 109 | 36 |
| 7. | Cervical Myelograph | 121 | 40 |
| 8. | Cervical spine PA & LAT | 120 | 40 |
| 9. | Chest/adult/PA | 60 | 20 |
| 10. | Chest/adult/PA & LAT | 120 | 40 |
| 11. | Chest/infant/AP | 50 | 10 |
| 12. | Chest/infant/PA & LAT | 100 | 25 |

| No | Services | PW Price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 13. | Cyst Uretrography | 114 | 38 |
| 14. | Dental X-ray | 100 | 40 |
| 15. | ECG | 70 | 30 |
| 16. | Fistulography | 121 | 40 |
| 17. | Foot | 60 | 20 |
| 18. | Forarm/Adult | 60 | 20 |
| 19. | Forarm/Infant | 40 | 10 |
| 20. | Fumer/adult | 60 | 20 |
| 21. | Fumer/Infant | 40 | 10 |
| 22. | GVU/IVP | 169 | 56 |
| 23. | Hand | 60 | 20 |
| 24. | Histography | 109 | 36 |
| 25. | Humorous | 60 | 20 |
| 26. | Joint Ankle | 60 | 20 |
| 27. | Joint Cervical | 60 | 20 |
| 28. | Joint Elbow | 60 | 20 |
| 29. | Joint Hip | 60 | 20 |
| 30. | Joint Knee | 60 | 20 |
| 31. | Joint Shoulder | 60 | 20 |
| 32. | Joint Wrist | 60 | 20 |
| 33. | Leg/ Infant | 50 | 10 |
| 34. | Leg/Adult | 60 | 20 |
| 35. | Lumbar Spine/Infant | 100 | 20 |
| 36. | Lumbar Spine/PA & LAT | 120 | 40 |
| 37. | Lumbar-Lumbar/Adult | 60 | 20 |
| 38. | Lumbo- Sacral/Adult | 120 | 40 |
| 39. | Mandible PA & LAT | 120 | 40 |
| 40. | Nasal bone | 60 | 20 |

| No | Services | PW Price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 41. | Pelvis/Adult | 60 | 20 |
| 42. | Pelvis/Infant | 50 | 10 |
| 43. | Sinus PA | 60 | 20 |
| 44. | Skull PA & LAT | 120 | 40 |
| 45. | Thoraco Spine PA & LAT | 120 | 40 |
| 46. | Thoraco Spine PA and LAT/ adult | 120 | 40 |
| 47. | Thoraco Spine PA and LAT/ child | 100 | 20 |
| 48. | Ultrasound | 90 | 20 |
| 49. | Fluoroscopy Exam | 350 | 50 |
| 50. | Electroencephalography (EEG) | 300 | 100 |
| 51. | CT | 350 | 200 |
| 52. | MRI | 400 | 250 |

## 8. Miscellaneous

| No. | Services | PW price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | Card/ outpatient Consultation Fee for Gps | 45 | 5 |
| 2. | Card/ outpatient Consultation Fee specialist | 60 | 5 |
| 3. | Inpatient senior Consultation per day | 50 | |
| 4. | IPD, Bed Day according to the class level | 100-120 | |
| 5. | Medical examinations Certificate | 45 | 5 |
| 6. | Physician Round per day per patient | 10 | |
| 7. | Physiotherapy procedures according to the level of intervention | 25-40 | |
| 8. | Nerve conduction study | 350 | 100 |
| 9. | Anesthetics procedure | 500 | 50 |

# የግል ህክምና አገልግሎት የትርፍ ክፍፍል

ከተጣራው የግል ህክምና ገቢ 70% ለጤና ባለሙያ 15% ለሆስፒታል እና ቀሪው 15% ለአስተዳደርና ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይውላል፡፡ ከሁሉም እኩል 1 አንድ በመቶ ተቀንሶ 3 በመቶ የግል ህክምና ክፍል ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በዚህም መሰረት የጤና ባለሙያው ድርሻ የሆነው 69 በመቶ ሰንጠረዥ /ሀ/ ላይ በተመለከተው መሰረት ለአስተዳደር ሰራተኞች ድርሻ 14 በመቶ በሰንጠረዥ /ለ/ ላይ በተመለከተው መሰረት የቁርጥ ክፍያ ተከፋዮች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ወደ 100% ተቀይሮ የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ ሀ**

| Sources of revanue | | | Specialist | GP | OPD Nurse | Lab. Professional | Radiographer | Radiologist | Anesthetist | anesthesiologist | OR and recovery Nurse | Assisstant | Ward Nurse | Pool |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 70% | | 25% | | | | | | | | | 5% |
| Consultation (Card) | | | | 70% | 25% | | | | | | | | | 5% |
| Laboratory | | | | | | 50% | | | | | | | | 50% |
| U/ saund | | | | | | | 10% | 70% | | | | | | 20% |
| x-ray | | | | | | | 55% | 25% | | | | | | 20% |
| Operation | | | 65% | | | | | | | | 10% | 10% | 5% | 10% |
| Nursing procedure | | | | | | | | | | | | | 70% | 30% |
| In patient | | | 40% | 35% | | | | | | | | | 25% | 5% |
| EKG | | | 40% | | 60% | | | | | | | | | |
| Indoscopy | | | 70% | | 30% | | | | | | | | | |
| Anesthesia | | | | | | | | | 80% | 20% | | | | |
| Pool | 80% | 70% medical/internal Med./ & GP | | | | | | | | | | | | |
| | | 30 % OBY/GYN and Surgen | | | | | | | | | | | | |
| | 15% | Nurse | | | | | | | | | | | | |
| | 5% | Pharmacy | | | | | | | | | | | | |





ሰንጠረዥ ለ

| | | |
|---|---|---|
| **Administrative staff** | | |
| Accountant | | 10.7% |
| Cash collectors | | 12.9% |
| Store man | | 2.1% |
| Main casher | | 2.1% |
| Cleaner | | 17.9% |
| Porter | | 9.3% |
| Laundry | | 5.7% |
| Lab assistant | | 1.4% |
| X-ray assistants | | 1.4% |
| Operator | | 1.4% |
| CSSD | | 3.6% |
| Registration | | 12.9% |
| Gard | | 9.3% |
| Miscellaneous * | | 9.3% |
| **Department Heads** | | ብር |
| **CEO** | | 2000 -2500 |
| **Medical Director** | | 1500 -2000 |
| **Private wing coordinator** | | 2000 -2500 |
| Finance Head | | 500 -1000 |
| Auditor | | 500 -1000 |
| Registration(MR) Head | | 300 |
| Cleaner's Head | | 300 |
| Gard/Security Head | | 300 |
| Driver's head | | 300 |

* እንደአስፈላጊነቱ ለአስተዳደራዊ ክፍያዎች የሚውል



